# እሸሩሩ ማሙሽ

የኢትዮጵያዊት እናት ኑሮ



እማ እንጣ!..

እ..ሽ..ሩ…ሩ… ማሙሽ…
ጓያውን ከክቼ…አልሜ ፈጪቼ …
በሙቅ ውኃ አቡክቼ…እንጨት ሰባብሬ…
ኩበትም ለቅሜ …ያንን አያይዤ …
ቂጣውን ጋግሬ …ጉርስ ለማሙዬ!…. እሽ?

እማ እንጣ!…

እ..ሽ..ሩ…ሩ…ሩ
ወፍጮዬን ወቅሬ …ክኬን እየፈጨሁ…
ለልጄ ለማሙሽ… ታሪክ አወራለሁ።

የማሙሽ ቅድመ አያት… ጅግና ነበር አሉ…
አምሳ አምስት ጥሊያንን… ማረከ ይላሉ።

አያቱ እንደዚሁ… ቀረ በዋለበት…
ወደ ስሜን ዘምቶ …በርስ በርስ ጦርነት።

መቼም ቅዱስ ገብሬል… መከራ አያልቅበት…
ሳይመለስ ቀረ… የማሙሽዬ አባት…
ባድማ ሲጠብቅ… ሾተል ተመዞበት።

በጦርነት ማለቅ… እድላችን ሆኖ…
ዛሬም በጭካኔ… ወጣቱ ተማግዶ…
ጥቂቱ ተታሎ… አብዛኛው ተገዶ…
ስንቱ በግ ተበላ…መቋደሾ ሆኖ።

እ…እ… እማ እንጣ! ….

አይዞህ… ማሙሽዬ…
የድህነት ልጄ….
እኔን ሙርሙር… ያርገኝ…
ጋም ብሏል ምጣዴ ….

እ..ሽ..ሩ…ሩ…ሩ
አምላክ ቢታደግህ…ይመጣል ወንድምህ…
ትምህርቱን ጨርሶ… ከርሃብ ሊያድንህ…
መንግስት ልቡ ራርቶ… ከስር ቢለቅልህ።

እ..ሽ…ሩ…ሩ ማሙሽ…
እኔ ጧትም ማታም… ጌታን እምለምን…
የማይገል መንግስት… መርቆ እንዲሰጠን።

ደሞም ጨቀጨቅሽኝ… አበዛሽ ካላለኝ…
ያንተን ክፉ ሳላይ… እኔን እንዲገለኝ!

እምጷ …. ጉረስልኝ የኔ ጌታ!


በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ተጻፈ ሚያዝያ ፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.
ሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ (አሜሪካ)